የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Federal Auditor General

ቁጥር / Ref. No OFAGF-03.13/ቀ/29
ቀን / Date 19/09/2013

ለተከበሩ አቶ አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል

ከላይ በርዕሱ እንደተጠቀሰው የ2012 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ የስራ አመራር ሪፖርት 48 ገጽ እና 25 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 82 ገጾች የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከማክበር ሠላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት

## የመደበኛ፡ የውጭ እርዳታና ብድር ገቢ ማጠቃለያ

## የ 2012 በጀት አመት

| ዝርዝር መግለጫ | ብር | ድምር |
|---|---|---|
| ሀ. መደበኛ ገቢ | | |
| ቀጥታ ታክስ | 64,130,900,161.48 | |
| ቀጥታ ያልሆነ ታክስ | 48,273,893,146.60 | |
| በውጪ ግብይት የሚገኝ ታክስ | 96,602,950,339.50 | |
| ከመንግስት ኢንቨስትመንት የተገኘ ገቢ | 17,285,062,469.31 | |
| ሌሎች ገቢዎች | 16,419,278,674.88 | |
| የመደበኛ ገቢ ድምር | | 242,712,084,791.77 |
| ለ. የውጪ እርዳታ | | |
| ከአለም አቀፍ ድርጅቶች እርዳታ | 56,489,838,417.36 | |
| ከመንግስታት የሚገኝ እርዳታ | 4,352,744,329.84 | |
| የውጪ እርዳታ ድምር | | 60,842,582,747.20 |
| የአገር ውስጥ ምንጮች | 332,047,261.57 | |
| የካፒታል ገቢ ድምር | | 332,047,261.57 |
| መ . የውጪ ብድር | | |
| ከአለም አቀፍ ብድር | 54,964,500,861.55 | |
| ከመንግስታት ብድር | 2,572,822,169.25 | |
| የውጪ ብድር ድምር | | 57,537,323,030.80 |
| ሠ. የአገር ውስጥ ብድር | | 62,510,908,085.00 |
| ጠቅላላ ድምር | | 423,934,945,916.34 |

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
## መንግስት
## የወጪ ማጠቃለያ

የበጀት ዓመት: 2012

(የገንዘብ መጠኖች በብር)

| የተወሰነ | መደበኛ ወጪ | ካፒታል ወጪ | ድምር |
|---|---|---|---|
| ጠቅላላ ድምር : | 209,513,924,533.77 | 159,268,799,365.63 | 368,782,723,899.40 |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 32,732,172,795.38 | 3,505,970,716.88 | 36,238,143,512.26 |
| የህግ አውጪና አስፈፃሚ አካላት | 1,538,458,995.13 | 369,172,344.23 | 1,907,631,339.36 |
| ፍትህና ደሕንነት | 7,427,540,676.67 | 1,244,026,885.77 | 8,671,567,562.44 |
| መከላከያ | 15,125,854,030.00 | 0 | 15,125,854,030.00 |
| ጠቅላላ አገልግሎት | 8,640,319,093.58 | 1,892,771,486.88 | 10,533,090,580.46 |
| ኢኮኖሚ | 6,128,881,298.01 | 48,228,071,230.51 | 54,356,952,528.52 |
| ግብርና እና ገጠር ልማት | 3,443,171,812.44 | 8,309,581,623.50 | 11,752,753,435.94 |
| ውሀ ሀብትና ኤነርጂ | 404,399,626.21 | 4,544,364,189.82 | 4,948,763,816.03 |
| ንግድና ኢንዱስትሪ | 700,295,498.52 | 649,891,465.10 | 1,350,186,963.62 |
| ማዕድን | 144,103,013.34 | 6,181,475.09 | 150,284,488.43 |
| ትራንስፖርት እና መገናኛ | 533,884,534.09 | 389,793,323.87 | 923,677,857.96 |
| የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን | 903,026,813.41 | 34,328,259,153.13 | 35,231,285,966.54 |
| ማህበራዊ | 44,212,043,357.18 | 36,504,048,699.64 | 80,716,092,056.82 |
| ትምህርት | 31,370,198,733.53 | 22,011,251,281.05 | 53,381,450,014.58 |
| ባህልና ስፖርት | 638,248,854.67 | 355,296,082.18 | 993,544,936.85 |
| ጤና | 5,112,071,127.09 | 14,099,218,844.45 | 19,211,289,971.54 |
| የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ | 173,362,172.98 | 22,253,661.59 | 195,615,834.57 |
| አደጋ መከላከል | 6,918,162,468.91 | 16,028,830.37 | 6,934,191,299.28 |
| ሌሎች | 22,349,187,865.95 | 23,619,538,734.95 | 45,968,726,600.90 |
| ሌሎች ድርጅቶች | 328,775,918.15 | 205,064,167.57 | 533,840,085.72 |
| ሌሎች የመዕከላዊ መንግስት ፕሮግራሞች | 22,020,411,947.80 | 23,414,474,567.38 | 45,434,886,515.18 |
| የክልል ድጎማ | 104,091,639,217.25 | 47,411,169,983.65 | 151,502,809,200.90 |

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት
## ወጪ እና የወጪ አሸፋፈን
## የ 2012 በጀት አመት

| ዝርዝር መግለጫ | ብር | ድምር |
|---|---|---|
| **1. ወጪ** | | |
| ሀ. መደበኛ ወጪ | | |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 32,732,172,795.36 | |
| ኢኮኖሚ | 6,128,881,298.01 | |
| ማህበራዊ | 44,212,043,357.18 | |
| ሌሎች | 22,349,187,865.95 | |
| የመደበኛ ወጪ ድምር | | 105,422,285,316.52 |
| ለ. ካፒታል ወጪ | | |
| አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት | 3,505,970,716.88 | |
| ኢኮኖሚ | 48,228,071,230.51 | |
| ማህበራዊ | 36,504,048,699.64 | |
| ሌሎች | 23,619,538,734.95 | |
| የካፒታል ወጪ ድምር | | 111,857,629,381.98 |
| ሐ. የክልሎች ድጎማ | | 151,502,809,200.90 |
| ጠቅላላ የወጪ ድምር | | 368,782,723,899.40 |
| ፋይናንስ | | |
| ሀ. የአገር ውስጥ ገቢ | | |
| የቀረጥ ገቢ | 209,005,731,829.12 | |
| ከቀረጥ ያልሆነ ገቢ | 34,758,068,688.64 | |
| የአገር ውስጥ ገቢ ድምር | | 243,763,800,517.76 |
| ለ. የውጪ እርዳታ | | |
| የአለም አቀፍ ድርጅቶች እርዳታ | 56,489,838,417.36 | |
| የመንግስታት እርዳታ | 4,352,744,329.84 | |
| የውጪ እርዳታ ድምር | | 60,842,582,747.20 |
| ሐ. የውጪ ብድር | | |
| የአለም አቀፍ ድርጅቶች ብድር | 54,964,500,861.55 | |
| የመንግስታት ብድር | 2,572,822,169.25 | |
| የውጪ ብድር ድምር | | 57,537,323,030.80 |
| መ. የአገር ውስጥ ብድር | | |
| ቀጥታ ብድር | 31,000,000,000.00 | |
| የግምጃ ቤት ሠነድ | 31,510,908,085.00 | |
| የተቀማጭ እና ሌሎች የሂሣብ ሚዛን | (56,811,075,416.58) | |
| የተጣራ የአገር ውስጥ ብድር ድምር | | 5,699,832,668.42 |
| ሠ የችሮታ ጊዜ ተከፋይ | | 939,184,935.22 |
| የፋይናንስ ድምር | | 368,782,723,899.40 |

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት
# የተጨማሪ ወጪ በጀት አሸፋፈን መግለጫ
# የ2012 በጀት አመት

| ዝርዝር መግለጫ | ብር | ድምር |
|---|---|---|
| 1. ወጪ | | |
| ሀ. መደበኛ ወጪ | | |
| የአስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት | 594,248,086.60 | |
| ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት | 694,198,081.65 | |
| ማህበራዊ አገልግሎት | 5,099,864,687.31 | |
| ሊሎች | 58,459,179,623.00 | |
| የመደበኛ ወጪ ድምር | | 64,847,490,478.56 |
| ለ. ካፒታል ወጪ | | |
| አስተዳደርና ጠቅላል አገልግሎት | 187,245,599.17 | |
| ለኢኮኖሚያዊ ልማት | 16,325,022,381.77 | |
| ለማህበራዊ ልማት | 8,585,285,495.72 | |
| ሊሎች | 187,245,599.17 | |
| የካፒታል ወጪ ድምር | | 25,097,553,476.66 |
| ጠቅላላ ድምር | | 89,945,043,955.22 |
| 2 የወጪ አሸፋፈን | | |
| ሀ. የአገር ውስጥ ገቢ | | 67,521,559,385.31 |
| ለ.የውጪ እርዳታ | | 18,980,509,733.09 |
| ሐ.የውጪ ብድር | | 3,442,974,836.82 |
| የፋይናንስ ድምር | | 89,945,043,955.22 |

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት

## የፋይናንስ አፈፃፀም መግለጫ

## ሰኔ 30 2012

የኢትዮጵያ ብር '000

| ዝርዝር መግለጫ | ማስታወሻ | 2012 | 2011 |
|---|---|---|---|
| **የመደበኛ ገቢ** | | | |
| የታክስ ገቢ | 4 | 209,007,743,647.58 | 176,057,050,170.35 |
| ታክስ ያልሆነ ገቢ | 5 | 4,328,078,181.21 | 3,094,033,239.14 |
| ሌሎች ገቢዎች | 8 | 28,682,705,551.57 | 25,169,770,146.17 |
| የመደበኛ ገቢ ድምር | | 242,018,527,380.36 | 204,320,853,555.66 |
| **የመደበኛ ወጪዎች** | | | |
| ለክልሎች የበጀት ድጋፈ | | 151,502,809,200.90 | 136,946,282,595.61 |
| ሰበአዊ ለሆኑ አገልግሎቶች | 9 | 52,145,524,926.10 | 8,923,147,532.58 |
| ዕቃዎች እና አገልግሎቶች | 10 | 48,696,197,714.40 | 19,909,763,369.27 |
| ቋሚ ንብረት እና ግንባታ | 11 | 74,669,097,842.95 | 33,681,349,238.83 |
| ሌሎች ወጪዎች | 12 | 20,739,288,689.39 | 10,940,427,695.25 |
| የመደበኛ ወጪዎች ድምር | | 347,752,918,373.74 | 210,400,970,431.54 |
| ትርፍ/(ጉድለት) | | (105,734,390,993.38) | (6,080,116,875.88) |
| **መደበኛ ያልሆኑ ገቢዎችና ወጪዎች** | | | |
| የውጪ እርዳታ | 13 | 60,842,582,747.20 | 44,693,188,343.11 |
| የውጪ ብድር | 14 | 57,537,323,030.80 | 31,193,706,677.55 |
| የካፒታል ገቢ | 15 | 332,047,261.57 | 84,457,035.26 |
| የብድር ክፍያ - ዋና ገንዘብ | 16 | 7,497,698,361.82 | 6,093,869,291.92 |
| የፋይናንስ ወጪዎች | 17 | 13,532,107,163.84 | 13,418,657,194.18 |
| ትርፍ/(ጉድለት) መደበኛ ካልሆኑ እንቅስቃሴዎች | | 97,682,147,513.91 | 56,458,825,569.82 |
| የዓመቱ ትርፍ/(ጉድለት) | | (8,052,243,479.47) | (46,030,239,795.88) |

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት
## የገንዘብ ፍሰት መግለጫ
## የበጀት ዓመት መጨረሻ ሰኔ 30/2012

| ዝርዝር መግለጫ | 2012 | 2011 |
|---|---|---|
| 1. ከመደበኛ እንቅስቃሴ የተገኘ ገንዘብ | | |
| የታክስ ገቢ | 209,007,743,647.58 | 178,985,605,265.66 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 4,328,078,181.21 | 38,701,729,123.19 |
| ሌሎች ገቢዎች | 28,682,705,551.57 | 14,780,141,864.27 |
| የተሰበሰበ ገቢ ድምር-ሀ | 242,018,527,380.36 | 232,467,476,253.12 |
| ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች | 52,145,524,926.10 | 42,968,742,363.73 |
| ለዕቃዎችና አገልግሎቶች | 48,696,197,714.40 | 41,994,369,518.72 |
| የፋይናንስ ክፍያዎች | 13,532,107,163.84 | 13,418,657,194.18 |
| የበጀት ድጋፍ | 151,502,809,200.90 | 136,960,401,583.31 |
| ሌሎች ወጪዎች | 21,638,471,933.48 | 27,422,744,614.51 |
| የክፍያዎች ድምር-ለ | 287,515,110,938.72 | 262,764,915,274.45 |
| በተከፋይ የተጨመረ/የተቀነሰ | 62,563,378,586.93 | 46,122,988,982.10 |
| በተሰብሳቢ የተጨመረ/የተቀነሰ | 42,510,394,971.61 | 16,452,276,719.14 |
| ገንዘብ ነክ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች | -6,059,944,610.28 | -52,510,302.65 |
| ገንዘብ ነክ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ድምር | 99,013,828,948.26 | 62,522,755,398.59 |
| የተጣራ የገንዘብ ፍሰት ከመደበኛእንቅስቃሴዎች | 53,517,245,389.90 | 32,225,316,377.26 |
| 2. የገንዘብ ፍሰት ከኢንቨስትመንትእንቅስቃሴዎች | | |
| ከንብረት ሽያጭ | 37,115,683.39 | 16,445,887.84 |
| ከብድር ክፍያ | 294,931,578.18 | 59,236,260.23 |
| የተሰበሰበ ገቢ ድምር-ሀ | 332,047,261.57 | 75,682,148.07 |
| ቋሚ ንብረት እና ኮንስትራክሽን | 74,669,097,842.95 | 69,063,306,712.10 |
| ከፕራይቬታይዜሽን | 0 | 2,257,496.28 |
| የክፍያዎች ድምር-ለ | 74,669,097,842.95 | 69,065,564,208.38 |
| የተጣራ የገንዘብ ፍሰት እንቅስቃሴዎች | 332,047,261.57 | (68,989,882,060.31) |
| 3. የገንዘብ ፍሰት ከፋይናንሺያል እንቅስቃሴዎች | | |
| ከውጭ ዕርዳታ የተገኘ | 60,842,582,747.20 | 48,151,319,865.13 |
| ከውጭ ብድር የተገኘ | 57,537,323,030.80 | 36,094,726,071.06 |
| የተሰበሰበ ገቢ ድምር ሀ | 118,379,905,778.00 | 84,246,045,936.19 |
| የውጭ ብድር ክፍያ የክፍያዎች ድምር ለ | 6,598,515,117.73 | 6,093,869,291.92 |
| ከፋይናንስ እንቅስቃሴ የተገኘ የገንዘብ ፍሰት | 111,781,390,660.27 | 78,152,176,644.27 |
| 4. በጥሬ ገንዘብ እና እንደ ጥሬ ገንዘብ በሚታዩ ላይ የተጣራ ጭማሪ/ቅናሽ | 24,944,963,532.93 | 8,483,057,522.94 |
| 5. በዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ ጥሬ ገንዘብ እና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚታዩ | 45,659,005,582.70 | 37,175,948,059.76 |
| 6. በዓመቱ መጨረሻ የነበረ ጥሬ ገንዘብ እና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚታይ | 70,603,969,115.63 | 45,659,005,582.76 |

መንግስት ሂሣብ ዳይሬክቶሬት

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት * Office of the Federal Auditor General

# ገንዘብ ሚኒስቴር

# የ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት

# የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ

# ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት/ 2013

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የገንዘብ ሚኒስቴር

## የ2012 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የገንዘብ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የገንዘብ ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ መግለጫዎች ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የገንዘብ ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የመደበኛና የውጭ እርዳታ ብድር ማጠቃለያ፣
- የወጪ ማጠቃለያ
- የወጪ እና የወጪ አሸፋፈን
- የተጨማሪ ወጪ በጀት አሸፋፈን መግለጫ
- የፋይናንስ አፈጻጸም መግለጫ
- የገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣

ገንዘብ ሚኒስቴር
Ministry of Finance

ማስታወሻ

memo

ለ፡- ሕዝብ ግንኙነትና ኢንፎርሜሽን ዳይሬክቶሬት

ከ፡- መንግስት ሂሳብ ዳሬክቶሬት

አለኸኝ መዋኸኝ
የመንግስት ሂሳብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ቀን፡- ሰኔ 08/2013 ዓ.ም

ጉዳዩ፡- **የ2012 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረገ ሪፖርት መላክን ይመለከታል፤**

2012 በጀት አመት የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ የገቢና የወጪ ሂሳብ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲት ተደርጐ የኦዲት ውጤቱ ግንቦት 19/09/2013 በተፃፈ የደብዳቤ ቁጥር OFAGF-03-13/1/29 ደርሶናል፡፡

በዚሁ መሠረት ውጤቱ በመ/ቤታችን ድህረገጽ ላይ እንዲለጠፍ የኦዲት ሪፖርቱን ኮፒ 9 ገጽ አያይዘን መላካችንን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

እንዲያውቁት፡-

- ክቡር የፊሲካል ፖሊሲ እና የፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ 08/10/13